# የፕሮፌሰሩን 'ሽምግልና' እንደ 'ሊትመስ ፔፐር'

ስለ ሽምግልና ታሪካዊ አመጣጥ ስለነበረውና ስለአለውም ፋይዳ መተንተን እናንተን ማስቸገር ነው። በሚገባ ታውቁታላችኋ! ይህ ድንቅ ባህል በተወላገደና በረከሰ መንገድ ሲሰራበት ግን ታላላቅ ዳኝነትን፣ እርቅንና ፍቅርን ያስገኘው ጥንታዊ መንገድ ጥላቻና መለያየትን አጎልብቶ ቅጥፈትን ዋጋ ሰጥቶ የሁዋልዮሽ መጉዋዝ ሲሆን ያሳዝናል፤ ሲደጋገም ግን ያስቆጣል። የስም አሰጣጡ ሽምግልና ሆኖ እንጂ ድለላ ተብሎ ቢሆን ኖሮ በእነ ፕሮፌሰር ኤፍሬም መደነቅም ባልኖረብን ነበር።

በቅርቡ ደደቢትኛን በአማርኛ በሚል አቶ አንዳርጌ የወያኔዎችን አዋጅ በቀላሉ ለመተርጎም የሚያስችል ቁልፍ አቀብለውን ነበር። እኔ ደግሞ ወያኔዎች ሲፈሩ የሚያሳዩትን ምልክት ልጠቁማችሁ ነው። ለምሳሌ ወያኔዎች ታሪካችን ሕዝባችን ማለት ከጀመሩ ፈርተዋል፣ ራእያችን፣ ሕዳሴ ሰላም ልማት ማለት ሲያበዙ ነገር አለ። ሽምግልና ምህረት እርቅ ሲሉ ግን ተወጥረዋል መርዙ እንዳለቀበት ኮብራ ሆነዋል ማለት ነው ልላችሁ ነው። ልክ መርዙን ማመንጨት ሲጀምሩ ግን ምላሳቸው ሁለትዮሽ ይረዝማል። የአይናችሁ ቀለም ከደበረን እንገላችኋለን ይሉናል። ውሾቻቸውም ጩኸታቸው ለጉድ ይሆናል፣ የጠሉትን ይነክሳሉ። ምን ያህል እንደታዘባችሁ አላውቅም እንጂ ሁኔታዎች ለወጥ ሲሉ ያለሰፈሩ የገባ ውሻ ጭራውን እንደሚቆልፈው ሁሉ እነርሱም መልመጥመጥ ይጀምራሉ፣ ሰላምታቸው በእጥፍ ያድጋል እብሪታቸውም ይተነፍሳል።

ፈሳሽ ውስጥ የሊትመስ ፔፐርን ጠለቅ ስታደርጉ እንደ pH መጠኑ ወረቀቱ ቀለሙን ይቀይራል። በዚህ መነሻ ነው መሰል የወያኔ ቤት ቀውጢ ሲሆን ብቅ የሚሉት ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሀቅን የወያኔ ቤት 'የሽብር ሊትመስ ፔፐር' የሚሏቸው የበረከቱት። እንደ እውነቱ ከሆነ የሰሞኑ የሽማግሌዎች ገባ ወጣም የዚሁ ምልክት ነው። በመጀመርያ ወያኔዎች አደራ ብለዋቸው ወደ ሽምግልና ውስጥ እንደገቡና አገልግሎት ሲሰጡ እንደነበረ በግልጽ የተቀመጠ ጉዳይ ነው። አሁን ደግሞ ብርትኳን እንድትዋሽ ለዚህም ሽማግሌዎቹ ውሸትን አጣፍጠው እንዲያቀርቡላት ተመክረው እንደነበረ ብርትኳን ግን እምቢ እንዳለች በድፍረት ይነግሩናል። ብቅ የሚሉበትን ጊዜና ሁኔታ ስንመለከተው ደግሞ ምን ያህል ለራሳቸው ክብር እንደሌላቸውና የኢትዮጵያን ሕዝብ የነጻነት ትግል ለመንጠቅና ትግሉን ለማኮላሸት የተለየ ተልዕኮ እንዳላቸው እንድንጠረጥር ያደርገናል። ዋሽቶ ማስታረቅ የሚል ፍልስፍና ይዘው ከሆነ ይህንን እርቅ ሳይሆን የተኩስ አቁም ስምምነት ቢሉት ነው የሚሻለው። የተኩስ አቁም ስምምነት አንደኛው ትንፋሽ እስኪገዛ ትጥቁን እስኪያጠባብቅ ድረስ ነው። ልክ በቅንጅት ላይ እንደደረሰው ማለት ነው። ሽማግሌዎቹ ሁኔታውን አረገቡለት በሁዋላ እድሜ ልክ ፈርዶ ወያኔ በአሸናፊነት ተወጣሁ እንዲል ሆነ። ከዚያ በሁዋላ ብርትኳን ስለእውነት በተናገረችበት ወቅት ሽማግሌዎቹ እንደ ጉም ተነኑና አሁን ወያኔ ሲወጠር እንደመስከረም ዝናብ ደንገት ዘነቡብን። ዘነቡልን አላልኩም ልብ አድርጉ።

አሁን ወያኔዎች የገቡበትን ጣጣ ቆጥሮ መጨረስ ያስቸግራል። መሰረታቸው ክፋት ስራቸው ደግሞ ጥፋት ስለሆነ ለአንደኛው ውሸታቸው የሚያደርጉት ጥገና ሰላሳ ውሸት እያስዋሻቸው ለራሳቸውም የዋሹትን እንኳ ማስታወስ እስኪያቅታቸው ሆኖባቸዋል። ግንቦት ሰባት ከሰማንያ አመት አዛውንት አንስቶ እስከ እምቦቃቅላ ሕጻናት ድረስ ዙርያቸውን የሚርመሰመስ ሆኖባቸው የሚያስሩትን የሚፈቱትን አያውቁም። ከመንግስት ግልበጣ እስከ ተራ ግድያ ድረስ ያሉ ወንጀሎችን በተመሳሳይ ሰዎች ላይ ለጥፈው በአለም ህዝብ ፊት ሲዘላብዱ መሳቂያ ሆነዋል። ለአረብ አገሮች መሬት ሲሰጡ አረቦቹ ደግሞ የኢትዮጵያን ምርት እንኳ ለመግዛት አንፈልግም ይሏቸዋል። ከቶኒ ብሌር ጉያ ተሰፈንጥረው አልብሽር ጓዳ መርመጥመጥ ይዘዋል። የጥምር መንግስት አቋቁሞ የነበረው ጠንቋይ ታምራት ገለታም ሕዝቡን አፍዝለን ብለው የሰጡትን ይዞ ወህኒ ወርዶአል። የቀሩት የመጨረሻ አማራጭ ፕሮፌሰሩ ይመስላሉ። ሊያዘናጉንና የውይይት አቅጣጫችንን ሊያስቀይሩን የኛ ተስፋ በርሳቸው መዳፍ ውስጥ ያለች እንዲመስል ሊያሳዩን ይሻሉ።

በሌላ በኩል የጥላሁን ገሰሰ ዜና እረፍትና የነበረው የቀብር ሁኔታ ታዋቂ ሰዎችን ትምህርት ያስተምራል ብለን የምናስብ ጥቂት አይደለንም። ጥላሁን ለብዙ ዘመናት ዜማ ስላቀነቀነ ብቻ አይደለም ሁላችንም የአለቀስንለት። ኢትዮጵያዊነትንና ሀገርን ከፍ አድርጎ ስለኖረ ነው። የሀገራችንን ሰንደቅ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረጉ ጀግኖቻችንን እንወዳለን። እነህ ጀግኖቻችንን ደግሞ ከሚወዳቸው ሕዝብ ጉያ ተሰፈንጥረው ራሳቸውን ሸቅብ ካወጡበት ሁዋላ መመለሻው ሊቸግር ይችላል። እኛ በጀግኖቻችን የሚጨክን አንጀት የለንም። ወያኔም ከህዝቡ ሊያርቃቸው ተግቶ መስራቱን በሚገባ እናውቃለን። ያለ እድሜውና እውቀቱ በታዋቂነቱ ብቻ የሽምግልና ጨዋታ ውስጥ የገባው እጅግ የምናከብረው ወንድማችን ኃይሌ ገብረሥላሴ ከዚህ ጉዳይ ውስጥ እጁን ካላወጣ ፈቅዶ የገባበት ጉዳይ ይሆንና ሕዝብ የሰጠው ፍቅር ወደ ጥላቻ፣ አክብሮቱ ደግሞ ወደ ንቀት ቢለወጥ ይቺ ቀን ስታልፍ ምነው በቀረብኝ ወደሚል ፀፀት የሚጨምረው እንዳይሆን ከወዲሁ

ማሳሰብ አስፈላጊ ይመስለኛል። ምኞቴና ጸሎቴም ወያኔዎች ገፍተው የጥላቻ ባቡር ላይ እንዳያሳፍሩትና ያውልህ ለየለህ ምን ትሆን? እንዳይሉት ነው። በዚህ አጋጣሚ ፓስተር ዳንኤል ከዚህ የድለላ ስራ ውስጥ እጃቸውን ካወጡ ጌታ ይባርካቸው።

በጠቅላላው ነገሮችን በአግባቡ መጠቀሙን ካወቅንበት የፕሮፌሰሩ ብቅ ማለት የትግሉን አንድ እርምጃ ወደፊት መሄድ አመላካች ነውና በያዝነው ሁሉ ልንተጋ ይገባል። ሁለቴ መበለጥ ግን ከየዋህነት ሳይሆን ከአላዋቂነት ያስቆጥራልና ብልህ እንሁን። በመጨረሻም የምለው ክቡር ሽማግሌዎች ሆይ ድለላን ከሽምግልና አንቆጥረውም። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ለነብሳችሁ ስትሉ በመጀመርያ ከእውነት ጋር ታረቁ። ለዚህም እግዚአብሄር ራሱ ይርዳችሁ ነው።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ